# ትግራይ ተጠቃሚ አይደለም ለሚሉ መልሴ ይኼው
# ጌታቸው ረዳ ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ
## ክፍል 1

በመጀመሪያ ሰሞኑን የጥምቀት በዓል ለማክበር በወጡ የወልድያ ኗሪዎች በወያኔ ትግራይ ፋሺስት ስርዓት ጥይት ለተገደሉ ዜጎቻችን ጽናቱን እና ብርታቱን እንዲሰጣቸው ለሟቾቹ ቤተሰቦች እና ለከተማው ማሕበረሰብ ጽናቱን ይስጣችሁ እላለሁ። ይህ ሃዘንና ግጭት በአማራ አካባቢ መድረሱን የሚያሳየን ለርዕሴ ይነተኛ ግልጽ የመከርያ ማስረጃ ነው። ስለሆነም በርዕሱ ላይ በጥልቀት እንመለከታለን። ርዕሱ በ2 ክፍል አቀርባለሁ። ይህ ክፍል 1 እንደመግቢያ ስለሆነ ዝርዝሩን በክፍል 2 ይቀርባል። በድረገጾች ትግራይ በዘመነ ወያኔ ተጠቃሚ ነው አይደለም የሚሉ ክርክሮች ወሩን በሙሉ ሲያከራክር መኖሩ ተመልክቻለሁ።በሌሎች ጉዳዮች ተጠምጄ ስለነበር ቀልብ አላደረግኩበትም ነበርና ዛሬ እተችበታለሁ።

ኢትዮ-ሚዲያ የሚባለው ድረገጽ ብዙውን ጊዜ አልጎበኘውም፤ ዛሬ፤ዛሬ አንድ ድረገጽ ከጎበኘህ ሁሉንም ማየት አያስፈልግህም። ምክንያቱም ሁሉም የሚለጥፉዋቸው ጉዳዮች ከአገር ውስጥ የሚያገኙዋቸው ጋዜጦች ከሚያወጡዋቸው ዜናዎች እየኮረጁ ስለሚለጥፏቸው ተመሳሳይነት ስላላቸው አንድ ድረገጽ በቂ ነው። እንዳውም ስንቶቻችሁ ታውቁ እንደሆነ አላወቅኩም እንጂ "Ethioexplorer.com" የተባለ ድረገጽ በየድረገጹና ራዲዮን ጣቢያዎች የተለጠፉት ሁሉ ሰብስቦ ባንድ ገጽ ርዕስ ርዕሶቹን ብቻ በማቅረብ መከፈቻ ቁልፎቹን በመጠቆም ወደ ኢመይልህ ስለሚልክ እየዞርክ ድረገጾችን ለማየት ጊዜ ከማጥፋት ያዳነኝ ይህ ታምረኛ ድረገጽ ዜናዎቹን በሙሉ ሰብስቦ ስለሚልክልኝ የምፈልገውን ብቻ እያነበብኩ ድረገጾችን ብዙውን ጊዜ ከመጎብኘት ስላዳነኝ Ethioexplorer.com" ካልዘገየኝ በስተቀር ኢትዮሚዲያም ሆነ ሌሎቹ አዘውትሬ አልጎበኛቸውም።

ይህ ካልኩኝ ዘንድ፤ ሰሞኑን ኢትዮ-ሜዲዮ ስጎበኝ አብርሃ በላይ በሚያካሂደው በዚያ ድረገጽ ውስጥ <u>ዶ/ር አወል አሎ</u> (ካሳሁን ከተባለ የኢሳት ጋዜጠኛ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ) እና <u>አቤ ተኩቻ</u> (ፌስ ቡክ/ብሎግ ይመስለኛል) ሁለቱም "የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሚ አይደለም"፤ወይንም "ያለው ስርዓት የትግሬዎች መንግሥት ሥርዓት አይደለም" ብለው ስለሚከራከሩ፡ አብርሃ በላይ የህችን የሚል ሰው ሲያገኝ "ደስታው የሰማይን ጣራ ስለሚነካ" የድረገጹ ማሸብረቂያ በማድረግ ሞቅ ባለ የትግርኛ ዘፈን በማጀብ **Activist warns against danger of lumping the Tigrai people with the ruling TPLF regime**
(By Ethiomedia January 15, 2018)
<u>**እና ሌላው ሁለተኛ ለመከራከሪያ ድጋፍ ያቀረበው ቪዲዮም Separate the wheat from the chaff: Tigrai people are no TPLF substitute!**</u> By Ethiomedia January 12, 2018 የሚል ርዕስ አበጅቶለት ቪዲዮውን አስደምጦናል። ተቃራኒ ያላቸው ሃሳቦች ግን ቢሞት አያስተናግደም። ጋዜጠኛ ብሎ ዝም!!!!

የነዚህ ወገኖች እምነታቸው የተጠበቀ መብት ሆኖ፤ መከራከሪያ ነጥባቸው ግን ልክ አብርሃ እንዳስቀመጠው 'እህሉ ከገለባው' መለየት አለብን ሲለን ዶ/ር አወል የተባለው ወጣት

ደግሞ “ሊሂቁ ከሕዝቡ ለይተን ማየት አለብን ሲል ተከራክሯል። የክርክራቸው ጭብጥ በዚህ ያጠነጠነ ነው። ጥልቅ መከራከሪያ ነጥብ አላስቀመጡም።

በዚህ ምዕራፍ 1 ጽሑፌ ኢትዮሜዲያ ባለቤት የሆነው የአቶ አብርሃ በላይ የጋዜጠኛነት ወገንተኛ ባሕሪ ሳልገልጽ ወደ ክርክር አላልፍም (የብዙዎቹ ውጭ አገር ያሉ ጋዜጠኞች ተብየ ድረገጾች ባሕሪ ተመሳሳይ ቢሆንም...)። የአብርሃ በላይ ለየት የሚያደርገው “ትግራይ ሕዝብ በዘመነ ወያኔ ተጠቃሚ ነው፤ወይንም ትግሬዎች በሥልጣን ላይ ናቸው”፤ ወይንም “ትግሬዎች እንደተቀሩት ማሕበረሰቦች ተመሳሳይ ግፍ እየደረሰበት አይደለም”፤ ወዘተ... የሚል ተከራካሪ የጻፈውን መከራከሪያ “ቢሞት” ድረገጹ ላይ አይለጥፈውም። የነዚህ ሁለት ወገኖች ግን አሽብርቆ ለጥፎላቸዋል። ይህንን በምሳሌ አስደግፌ ወደ ክርክር ልለፍ (ስንነጋገር ሕዝቡና የታሪክ ማሕደር እንዲያውቀው ማድረግ የግድ ስለሆነ አብርሃ በላይ በልምድ ያገኘው ጋዜጠኛነት ሙያው ለተጠቃሚው ሕዝብ ከተጻራሪ ክፍል የሚሰጡ አስተያየቶች እና አስተምህሮዎች ለድርገጹ ጎብኚዎች እኩል ያስተናግዳል ወይስ እንደ ወያኔዎች ወገንተኛ አገልግሎት ብቻ የተመረኮዘ አሰራር? የሚለውን በማስረጃ እንናንተ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ታሪክም አብሮ እንዲዘግበው ላቅርብ።

አብርሃ በላይ የማይወዳቸው (እራሱም ሆነ ሌሎች እንዲከራከሩበት የማይፈቅድ) ነጥቦችን ላስጨብጥ። “የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሚ ነው” ወይንም “ስርዓቱ የትግሬዎች መንግሥት ነው” የሚሉ ወይንም “ኦሮሞዎች የድሮ ስማቸው “ጋላዎች” ይባሉ ነበር፤ ስለሆነም “ጋላ” ማለት ስድብ አይደለም። ስድብ ነው ብለው ያለ ምንም ማስረጃ ሕዝቡን የሰበኩትና ያወናበዱት “የኦሮሞ ሊሂቃኖች/መኢሶን እና ኦነጎች” ናቸው”፤ “ጋሎች” በ16ኛው ክፍለዘመን የዛሬትዋን ኢትዮጵያን ወርረው የብዙዎቹ ነባር ከተሞችና አካባቢዎች ስም ሰርዘው የኦሮሞ ስም ሰጥተው ዝርያቸው አሁንም በተጠቀሱት አካባቢዎች ዛሬም ይገኛሉ፡፡” የሚሉ ተከራካሪዎች፤ ወይንም የሚሉ የታሪክ ጸሐፍትን እና ጽሑፎችን በድረግጹ አያስተናግድም። ይህንን በማስረጃ ለዶ/ር አሰፋ እና ለ ዶ/ር ጌታቸው ሃይሌ ምን ብሎ እንደጻፈላቸው በማስረጃ ላቅርብ።

እንሆ፤ አብርሃ በላይ ለሁለቱም ግዙፍ ምሁራኖች ክርክራችሁን አላስተናግድም ብሎ ከ7 አመት በፊት በኢመይል የጻፈውን ማስረጃ እንዲህ ይላል።

**From:** Editor <editor@ethiomedia.com> **Date:** 19 april 2012 08:44:30 CEST

Dear Dr Assefa Negash,

My apologies for my delayed response! To begin with, this short reponse shouldn't in anyway be mistaken for an invitation to engage you in a dialogue over the differences you and I've over the situation in Ethiopia. For instance, a sentence from your piece reads: "In present-day Ethiopia the only people who are not adversely affected by this rule are the Tigreans who as members of the ruling Tigrean

regime have every right to settle in every part of Ethiopia and prosper even at the expense of others."
We are worlds apart, brother.

For you, TPLF means the Tigrai people and vice versa. Though I wrote for years to persuade fellow compatriots like you that the ruling class is strictly an anti-Ethiopia mercenary class, such literature has fallen on deaf ears because brothers like you have made up their minds that Tigrians are in power and the people of Tigrai are beneficiaries of the 'Tigrian regime' That is the whole point in a nutshell. But again, you are entitled to your opinion as I'm to mine. I'm not going to post your article because I believe - with all due respect - your article is not only wrong but also misleading, and detrimental to the unity of the Ethiopian people.

I'm writing this as an Ethiopian journalist, and not because I was born into a Tigrian family. I would have rejected (and I've done it several times in the past) if I were asked to post an article that in anyway tarnishes the image of the Amhara, Oromo etc people. For instance, a few days ago, an article written by Prof Getachew Haile about the Oromo people was removed from our website shortly after it was posted because there were lines that cast our Oromo people as 'invaders' and much worse. I hope such denial of service wouldn't in any way strain our friendship.
Warmest regards,
Abraha Belai, Editor

ደ/ር አሰፋ ነጋሽ (አምስተርዳም ኗሪ) **Why Have the Amaras Once Again Become Victims of Ethnic Cleansing by TPLF?** የሚል **ከእስር ቤት የተላኩ** ዘርን ያነጣጠሩ በርካታ ሰቆቃዎች የሚያጋልጡ የተላኩ ሰነዶችን ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ ለመላ ሚዲያዎች የተላከውን ለኢትዮሚዲያም ጭምር የአማራ ሕብረተሰብ ሰቆቃ ለመላው ዓለምና ለሕዝባችን ለመንገር በመረጃ የተዘጋጀ እንዳይሰራጭ ያገደበት ምክንያት መልስ ሲሰጥ የሰጠው ምክንያት ከላይ እንደተመለከታችሁት በራሱ ቃል “brothers like you have made up their minds that Tigrians are in power and the people of Tigrai are beneficiaries of the 'Tigrian regime.'

ይላል። ስለሆነም ትግሬዎች ሥልጣን ላይ ሳይወጡ ሥልጣኑን ተቆጣጥረውታል ማለትህና፤ትግሬዎች በዚህ ሥርዓት ተጠቃሚ ሳይሆን ተጠቃሚ ነው…" የሚል እምነት ስለያዝክ "አልለጥፍልህም!" ሲል ማጠቃለያ ምክንያቱ ይህ ብቻ መሆኑን ገልጾለታል። that is the whole point in a nutshell. ሲል በግልጽ አምቢታው ግልጽ አድርጓል። ለዚህም የማጠቃለያ ክርክሩ <<your article is not only wrong but also misleading, and detrimental to the unity of the Ethiopian people.>> አንባቢን ማሳሳት ወይንም እንዲህ ማለት ስህተት ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱ አንድነት አፍራሽ ነው" ሲል ስሕተትነቱንም ሆነ አገር አፍራሽ መሆኑን ግን ሊገልጽ አልቻለም። ብዙዎቹ ተከራካሪዎቻቸው የሚጠቀሙባቸው የተለመዱ ድፍን ያሉ መልሶቻቸው በዚህ ዙርያ ያጠነጠኑ ናቸው።

ትግሬዎች ሥልጣኑን ተቆጣጥረውታል ለማለት "አማራን ሰቆቃ" ምክንያት አድርገህ በሽፋን የመጣኸው 'በወያኔ ዘመን ትግሬዎች ተጠቃሚዎች ናቸው፤ ትግሬዎች ሥልጣን ላይ ናቸው" ለማት ስለፈለግክ ነው" ሲል ጽሑፉን ላለማተም አብርሃ የሰጠው ምክንያት ያ ነበር።

ለፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌም ጹሑፋቸው ከድረገጹ እንዲነሳ የሆነበት ምክንያትም ከላይ እንደነገርኳችሁ "የታሪክ ምሁራንም ሆኑ ምሁራን ባጠቃላይ ግራይ ወረራ ተከትሎ 'የ16ኛው ክ/ዘመን ጋላዎች" ኢትዮጵያን ወርረዋል ስላሉ አልለጥፍልህም ብሏል። የሚገርመው እና አሳሳቢ ሊሆን የሚችለው፤- አቶ አብርሃ በላይም ሆነ መሰሎቹ በወደፊትዋ ኢትዮጵያ ይህንን ርዕሶች በሚመለከት የሚወጡ ጹሑፎችና መጽሐፍቶች አሳታሚ ወይንም የሳንሱር ክፍል ሚኒስቴር ቢሆን በዩኒቨርሲቲ ተቋማት ውስጥም እንዳይታተሙና ውይይት እንዳይደርግም ይከለክል እንደነበረ መገመት አያስችግርም።

ይህንን ወገናዊነትን ለተወሰኑ ወገኖች በመፍቀድ የድረገጹ ተጠቃሚዎች የሆኑትን ግለሰቦች ትግሬዎች የስርዓቱ ተጠቃሚዎች አይደሉም ወይንም ስርዓቱ የትግሬዎች አይደለም የሚሉ ተከራካሪዎችን በሙዚቃ እና በራሱ አዘጋጅነት የቀረቡ 'አጫጭር ስዕለ ድምጽ ማስረጃዎን/ክሊፖችን' ትግራይ ውስጥ የሚኖሩ የትግራይ ኗሪዎች የሚያሰሙትን የመጥፎ አስተዳዳር እሮሮዎችን ወደ አማርኛ ተርጉሞ በሙዚቃና በቪዲዮ አጅቦ ለነዚህ ተከራካሪ ወገኖች የሚሆን ድጋፍ እያቀነጃጀ እንድናደምጣቸው አድርጓል።

በዶ/ር አወል አሎ ልጀምር። 'ሕዝብ እና መሪዎች ለይቶ አለማየት የፖለቲካ ስሕተት ከመሆኑ ሌላ ሕዝቡ ወጥቶ መሪዎቹን አልተቃወማቸውም የሚለው መከራከሪያ ሌሎቹስ መቸ ወጥተው ሲቃወሙ አየን" ይላል ደ/ር አወል።

ለዚህ አጭር መልስ ሰሞኑን እንኳ ወልድያ ላይ የታየው ተቃውሞ እና ግብግብ ለዶ/ር አወል እና መሰሎቹ አንድ ማሳያ ማስረጃ ነው።

እነ አብርሃ በላይም ሆኑ እነ ዶ/ር አወል እና አቤ ቶከቻው የመሳሰሉ መከራከሪያቸው ጥልቀት የለውም። ምክንያታቸው መከራከሪያችንን በበቂ እና አሳማኝ ማስረጃ ሊመክቱ አይችልም። "ትግሬዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹስ መቸ ወጥተው ሲቃወሙ አየን የሚለው ከዶክተሩም ሆነ ከሌሎች ሰዎች የሚደመጠው ምክንያታዊ መከራከሪያቸው እኔም ሆንኩኝ ሌሎች ትግሬዎች (ለምሳሌ የሕግ ጠበቃ ሙሉጌታ አረጋዊ) አስቀድመን ያልነው መከራከሪያ

ነበር። ያ ነጥብ ብዙም የሚያስኬድ ባይሆንም፤ እኔም ያልኩበት ወቅት ለመግለጽ ካስፈለገ “ትግሬዎችን በጥላቻ ተነሳስተው ሁላችሁንም እንፈጃለን” ሲሉን ለነበሩ አንዳንድ ሰዎች ከበርከታ አመታት በፊት በፓልቶክ ባደረግኩት ቃለ መጠይቅ የሰጠሁት መከራከሪያ ነበር። ሆኖም ያ መከራከሪያ ጊዜው ያለፈበት እና አሁን ካለው ሁኔታ የሚሄድ አይደለም። እኔም አልጠቀምበትም። ድሮም ቢሆን ወያኔን ከሚቃወሙ የትግሬዎች ቁጥር አንጻርና የወያኔ ደጋፊዎች ከተቃዋሚው ብዛት አንጻር ሲነጻጸር ‘ትግሬዎች” ከመጀመሪያ ጀምሮ ለብዙ አማታት የወያኔ ደጋፊዎች ሆነው ቆይተዋል የሚል መከራከሪያየ በቃለ መጠይቅም ሆነ በጽሑፎቼ ያቀረብኩት መከራከሪያም ታሳቢ ይሁንልኝ።።

ያም ይሁን ብንልም፤ ማለትም “ትግሬዎች ብቻ ሳይሆኑ” “ሌሎቹም ሲቃወሙ አልታዩም” ሲባሉ የነበረው መካረከሪያ ጊዜው ያለፈበት ነው የምለውም ምክንያት ‘ዛሬ መላው አገሪቱ በሚባል መልኩ” ጸረ ስርዓቱ ተነስተው በደም እየተፋለሙ፤በሺዎች የሚቈጠሩ በጦር ካሚዮኖች እየታፈሱ ወደ ሲኦል እስር እየተጋዙ ነው (የሰሞኑን የወልድያው ተቃውሞና ጭፍጨፋ ዓይነተኛ የቅርብ ማስረጃ እንደ ጭብጥ ያዙልኝ)። እዛም ሲደርሱ ወንዶቹ በላያቸው ላይ ሽንት እየተሸናባቸው ፤ ሴቶች ደግሞ እርቃናቸው ወጥተው እየተገረፉ ገራፊዎቻቸው አረቄ እየጠጡ ሲያሸማቅቅዋቸውና ሲደፍሯቸው፡ ወንዶች ደግሞ ብልታቸው ተኮላሽቶ ዘላለማዊ ሕይወታቸው እንዲበላሽ እየተደረገም ቢሆን በዛው ሁኔታ ሆነው የተቃውሞ እያሰሙ ፊት ለፊት ተፋጥጠው የአንገዛም እምቢታ እያሰሙ በመቆም ወያኔዎችን እያስጨነቁ ነው። ወንዶች በየ እስር ቤቱ በወያኔ ግብረሰዶማውያን እንዲደፈሩ ተደርጓል። ትግሬዎች ላይ እንዲህ አልደረሰም። ደረሰ ከተባለም በሕዝባዊ እምቢታ አልተጋፈጡትም።

ትግሬዎች በደል ሲደርስባቸው ልክ እንደሌሎቹ ተቃውሞአቸው “ሆ!!” ብለው በቀጣይ እያስሰሙም። እየተቃወሙ ነው ከተባለስ <<በቃ! ከዙፋኑ ውረድ!>> የሚል ተቃውሞ ነው የሚያስሙት ወይስ መብራት እና የውሃ ቧምቧ በከተማችን አልተስፋፋም፤ አስተዳዳሪዎች የነቀዙ ናቸው፤…>>፡ የሚሉ  አቤቱታቸው? ወይስ ትግሬዎችስ ሲታሰሩ ልክ እንደ “አማራ’ ሴቶች እራቁታቸው አስወልቀው አረቄ እየጠጡ ያሰቃይዋቸዋል? ይደፍርዋቸዋል? በነገዳቸው ይዘልፏቸዋል? በወንዶች ላይሰ በላያቸው ላይ ሽንት ይሸኑባቸዋል? ግድግዳ ግፋ! ትግሬ ማለት የማይገፋ ግድግዳ ማለት ነው እየተባሉ ግድግዳ እንዲገፉ ይደረጋሉ?

ለዶክተር አወልም ሆነ ፤አቤ ተኩቻው እና ለነ አብርሃ በላይ አንድ ጥያቄ ልጠይቅ እና ዶ/ር አወል የኛ ትንታኔ ስሕተተኛ መሆኑን ሲገልጽ “<u>ከፖለቲካ ትንታኔ አንጻር ፍጹም የተሳሰተ ነው”</u> ሲለን  ምን ማለቱ ነው? ይህ ትንታኔ ሰሞኑን በሁለተኛ ክፍል ስለማቀርበው በዚህ ክፍል ግን ከላይ የጠቀስኳቸው ሰቆቃዎች እና ጥያቄዎች ግልጽ እንዲሆኑላቸው ጥያቄየ የሚከተለው ነው። ይህ ጥያቄ የተመረኮዝኩት “ብዙ ፍዳ ደርሶበት እና በሌሎችም ያያውና የሰማው አሰቃቃ የግርፋት ስቃይ አይቶ ዛሬ ከእስር ተፈትቶ እኛው ጋር አብሮን እዚህ የሚኖሮው የቅንጅቱ ሓብታሙ አያሌው ከተናገረው ልጥቀስ እና እነዚህ ወንድሞቼ እንዲመልሱልኝ እጠይቃለሁ። ሓብታሙ አያለው እንዲህ ሲል ስለ ወያኔ ገራፊዎች ይናገራል፡-

<< እስር ቤት ውስጥ ያሉ ገራፊዎች <u>99%</u> ትግርኛ ተናጋሪዎች ናቸው። ሲገርፉም በተለያየ ጊዜ እንደተናገርኩት ትግሬ ማለት እንደዚህ ነው፤ ግድግዳ ግፋ እያሉ ሲያስገፉን ይቆዩና እየሞከራችሁት ያላችሁት ይሄንን ነው፤እኛ ማለት እንደዚህ ነን (የማንገፋ ግድግዳዎች) እያሉ ‘ወከለው (እኛ ትግሬዎች እያሉ) ነው የሚነግሩን።  እና በዚህ አጋጣሚ አንድ

መልእክት ለማስተላለፍ እፈልጋለሁ። በቅርቡ ህጻናትና አሮጊቶችን በጥይት እየቦደሱ ሰው እየገደሉ ኢያሉ ሰዎች ያችን አገር እየገዙ እንዳይቀጥሉ ከተፈለገ፤ ጎጃም ላይም ጎንደር ላይም፤ጅማ ላይም ወልቅጤ ላይም፤ጋምቤላም፤ቤንሻንጉል ላይም፤ በየትኛውም ቦታ ደረቱን በጥይት ለተመታ ለሞተው ልጃቸው ለሐዘን አደባባይ ሲወጡ አሮጊቶች መገደላቸው፤ መቀሌ ላይም ከተሰማ "እባካችሁ" ስለ ኢትዮጵያ አምላክ እንዚህን ልጆች "የኛ ልጆች ኢይደላችሁም "በቃን!" በልዋቸው።" ብየ መልእክት ለትግራይ ሕዝብ አስተላልፋለሁ።>> <<፡ማሕሌት ካሳሁን እና ኤዶም ካሳየ ወጥተው ለሚዲያ ተናግረዋል። ሌለት እራቁታችንነ አስወልቀው ስፖርት ያስሰሩን ነበር፡ አሉ። በእነ ዘመነ ምሕረት ገላ ላይ ሽንታቸውን የሚሸኑ። ወንድ ልጅን እግር እስጃቸውን አስረው ከላቸው ላይ የሚሸኑ ገራፊዎች ! እነዚህ ኢትዮጵያዊያን አይደሉም። ከሰብአዊነት ውጭ የወጣ ነው።>> (*ሓብታሙ ኢያሌው ለሕዝብ ከተናገረው የተገኘ አውድዮ ቪዲዮ ምንጭ ዩ ቱብ።*)

አሁን እነ ዶ/ር አወልም እነ አብርሃ በላይም እነ አቤ ተኩቻውም እና መሰል ተከራካሪዎች ተመልሼ እነዚህን ወንድሞች የምጠይቃቸው 'ሓብታሙ ኢያሌው' የጠየቀውን ቀጥተኛ ጥያቄ ነው መልሼ የማስተጋባው።

<<ጎጃም ላይም ጎንደር ላይም፤ጅማ ላይም ወልቅጤ ላይም፤ጋምቤላም ቤንሻንጉል ላይም፤በየትኛውም ቦታ ደረቱን በጥይት ለተመታ ለሞተው ልጃቸው ሐዘን አደባባይ ሲወጡ አሮጊቶች መገደላቸው፤ መቀሌ ላይም ከተሰማ "እባካችሁ" ስለ ኢትዮጵያ አምላክ *እንዚህን ልጆች "የኛ ልጆች ኢይደላችሁም "በቃን!" በልዋቸው።"* ብየ መልእክት ለትግራይ ሕዝብ አስተላልፋለሁ።>> ሲል ሓብታሙ ለትግራይ ሕዝብ ያስተላለፈው ጥያቄ የትግራይ ሕዝብ እባካችሁ ልጆቻችሁ እንዲህ ያለ ፍዳ በዜጎች ላይ እፈጸሙ ነው *እና 'ሊጆቻችን ኢይደላችሁም በቃን! በሉዋቸው* ሲል የትግራይ ሕዝብ እየተደረገ ላለው ግፍ ጆሮ አልሰጠውም፤ ዝምታን መርጧል፤ እያለን ነው። እባካችሁ ልጆቻችሁን በቃችሁ በልዋቸው፡ ነው እያለው ያለው። የሰሞኑን የወልድያው ጭፍጨፋ እና ተቃውሞ ከዚህ መከራከሪያ ጋር ጨምሩበት። እንዲህ ያለ ሕዝባዊ አምቢተኛነትና የተከተለው ጭፍጨፋ ትግራይ ውስጥ እየተደረገ ነው ወይ?

ይህ ሁሉ ግፍ ሲፈጸም ምንድ ነው ዝምታው? የሚል ነው መልእክቱ። ታዲያ ይህ ጥያቄ የሃብታሙ ብቻ ሳይሆን የብዙ ዜጎች ድምጽ እና አቤቱታ ነው።በቃን ብላችሁ ደርግን ተዋግታችሁ እንዳስወገዳችሁት "ልጆቻችሁም" በቃችሁ ብላችሁ ከዚህ ፍዳ ለመውጣት እናንተም ተባበሩን፤ ድምጽ ሁኑን፤ የምትለግሱት የሞራልም ፤የመንፈስም ሆነ የቁሰቁስ እርዳታም ከዚህ ወዲያ አንለግስም ፤"በቃችሁ!" በልዋቸው ነው እየተባለ ያለው። የትግራይ ሕዝብ አደባባይ ወጥቶ እንደተጠቀሱት አከባባዎች ኡ@ ኡ@!!! እያለ ቢጮህ ኖሮ *በኢትዮጵያ አምላክ እባካችሁ* እያሉ የትግራይን ሕዝብ ትብብር "ልመና" አይተላለፍም ነበር? አደልም እንዴ?

ትግሬዎች እንደሌሎቹ አካባቢ ሕዝብ ይፋ የሆነ ተቃውሞ ለምን አላሳዩም ብየ ስጠይቅ እነ ዶክተር አወል የነሚነግሩን ዛሬም "ፍርሃት አለው፡ ነው። ፍርሃታቸው ምንድ ነው? ተብሎ ሲጠየቁ ደግሞ ዶ/ር አወል የሚለን "ያ ሕዝብ በተለያዩ ሁኔታዎች በተለያዩ ፍርሓቶች ውስጥ እንደገባ የተደረገ ነው፤ መሪዎቹ ከሥልጣን ከተወገዱ ሕዝቡም አብሮ እንደሚጠፋ ስለተሰበኩ መቃወም አልፈለጉም፡ ስለዚህም ያንን ሕዝብ "ብሌም""(መውቀስ) መሰረታዊ ችግር ያለበት ነው።>>፡ ነው መከራከሪያቸው። እነ ዶ/ር አወል ሕዝቡ ስርዓቱን ለመጣል

በፍርሓት ምክንያት እንደማይቃወም ግን አምነዋል። እዚህ ላይ ‘ሕዝቡ ሰርዓቱን አልቃወምም ብሎ ዛሬም ዝም ብሏል” የምንለውን ክርክራችንን ግን ማመናቸው አስምሩበት።

የአቤ ቶኩቻው የብርሃ በላይ እና የአብርሃ ደስታ መከራከሪያ ደግሞ

<< እዚህ አውጭ አገር “አይበልናንዶ” የሚሉት ተሓህትን የሚደግፉ በየፌስ ቡኩና ውር ውር የሚሉት አይደሉም ትግሬዎቹ ፤ትግሬዎቹ ተራራን እየቧጠጡ በድህነት እየማቀቁ ያሉ ናቸው ትግሬዎቹ>> ሲል ይከራከራል። <<“ወያኔዎች እንጂ ትግሬዎች ሥልጣን ላይ አይደሉም፡ እንዲያ ለሚሉት ተከራካሪዎች አገር አደጋ ላይ እየጣልዋት ነው ሲሉ “አክቲቪስቶች” ማስጠንቀቂያ እየሰጡ ነው>> (አብርሃ በላይ- ኢትዮ ሚዲያ)>> <<የግለሰብ አፓርታይድ እንጂ ወያኔ አፓርታይድ አይደለም >>(አብርሃ ደስታ -የዓረና ፓርቲ መሪ) የመሳሰሉትን ክርክሮችን እንመልከት።

“ስርዓት ላይ ያለው የትግሬዎች ስርዓት ነው”፤ “ትግሬዎች በቂ ተቃውሞ አላሳዩም”፤ “የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ናቸው” የምንል ሰዎች የኢትዮ-ሚዲያው አብርሃ በላይ እየወነጀለን ያለው “የትግራይ ሕዝብ የስርዓቱ ተጠቃሚ ነው እያሉ የትግራይን ሕዝብ የሚወነጅሉ ሰዎች አገር ለአደጋ እያጋለጧት ነው” ተብለን በማስጠንቀቂያ ርዕስ (ዋርኒነግ) ተከሰሰናል፤ በማን? በአብርሃ በላይ። አገርን ለአደጋ እያጋለጥዋት ናቸው ብለው የሚከስሱን ደግሞ አብርሃ በላይ እና እራሱ አብርሃ “አክቲቪስቶች” የሚላቸው ድረገጹ ላይ የለጠፈላቸው ከላይ የተጠቀሱት ተከራካሪ ሰዎች ናቸው።

የዶ/ር አሎም “ፖለቲካዊ ስሕተት ስለሚለው” በሁለተኛው ክፍል ጽሑፌ ስለምገልጸው፤ያንን ላቆይ እና አቤ ቶኩቻ ላይ ትንሽ ልበል።

እነዚህ እውጭ አገር ያሉትንም ሆነ አገር ውስጥ ያሉት የወያኔ ደጋፊዎች የስርዓቱ ተጠቃሚዎች/ደጋፊዎች “ትግሬዎች” አይደሉም ሲል ይነግረናል። እነዚህ ትግሬዎች ካልሆኑ ነገዳቸው ምንድ ነው? ከየት ክፍለሃገር ነው የመጡት? ገጠር ያሉት ትግሬዎች የነዚህ ወላጆች፤ እህቶች፤ ወንድሞች፤ ዘመዶች አይደሉም? እንዲያው ለመሆኑ 160 ሺ ታጋዮች የቆሰሉ እና 65 ሺ የሞቱ የወያኔ ታጋዮች ትግሬዎች ካልሆኑ ምንድ ናቸው? በሕይወት ያሉት በ100 ሺዎች የሚቆጠሩ ታጋዮች እና የነሱ ወላጆች ዘመዶች እንዲሁም በሚሊዮኖች የትግራይ ኗሪ ደጋፊዎቻቸው ትግሬዎች ካልሆኑ ምንድ ሊሆኑ ይችላሉ?

እነዚህ ወንድሞች የሚያቀርቡት ምክንያት፡-

<“በመብት ጥሰት” እንደሌሎቹ ነገዶች ልክ በፍትሕ ዕጦት የተበደለ መሆኑንና አንዳንዶቹ በከፋ መልኩ ግፍ እየተፈጸመባቸው መሆኑን ነው እንደመከራከሪያ የሚያቀርቡት>። አብርሃ በላይ እና ለነዚህ ተከራካሪ ወንድሞቻችን ማጠናከሪያ ማስረጃ እንዲሆን ባንዳንድ የትግራይ ከተሞች/ወረዳዎች የተደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎች የተሰሙ እሮሮረዎችን እንደ ማስረጃ አድርጎ ኗሪዎቹ ለወያኔ ወኪሎች የተናገሩትን ወደ አማርኛ በመተርጎም ለክርክሩ ማስደገፊያ ማስረጃ አድርጎ የቪዲዮ ማስረጃው አመኔታ እንዲኖሮው አድርጓል። በቪዲዮው የቀረበው እንደ ሌሎቹ አካባቢ ሕዝብ አደባባይ ላይ ወጥቶ አስፋልት ዘግቶ፤ ስራ አቁሞ “ስርዓቱን ከሥልጣን” ውረድ የሚል ቢሆን ኖሮ መከራከሪያ ነጥብ በሆነ ነበር። ግን

ባለሥልጣኖቹ የነቀዙ መሆናቸውን ለከፍተኛ ባለስልጣኖች ስሞታ የሚያሰሰሙት አቤቱታ እንጂ ሕዝባዊ ተቃውሞ አይደለም። ሕዝባዊ ተቃውሞ ምን ማለት እንደሆነ አንባቢዎቼ የምትፈርዱት ይመስለኛል። “ወያኔ ሌባ! ወያኔ በቃህ! ከስልጣን ውረድ! ሰንደቃላማችን ይህች ናት!...” የሚሉ ትግራይ ውስጥ አልተሰሙም። ለምን?

ቢሆንም አብርሃ በላይ ያቀረበው የቪዲዮ ክሊፕ ማስረጃ እንደ ሕዝባዊ እሮሮ ማሳያ የመቀበል ችግር የለኝም። ችግር የሚሆኖው ከነባራዊው ሁኔታ የተገናኘ ብቻ ሳይሆን መከራከሪያው ከፖለቲካ አንጻር ምሁራዊ ትንታኔ የጎደለው ክርክር ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እያልኩ ያለሁት ‘ሕዝባዊ አመጽ አይደለም’ ነው እያልኩ ያለሁት፡ እሮሮ ነው፤ ዛቻ ነው ሲሰማ የነበረው፡ ያ የኗሪዎች በባለጉት አካባቢ ሹሞች ላይ የተደመጠ “የዛቻ ድምጽ/ማስጠንቀቂያ” ወደ ተግባር ይለወጥ ነው እያልኩ ያለሁት።

ሌላው መሰመር ያለበት ጉዳይ፤- አብርሃ በላይ፤አበበ ተኩቻው፤ዶ/ር አወልም ሁሉም የሚስማሙበት “ትግሬዎች የወያኔ ደጋፊዎች ናቸው ወይንም ነበሩ” የሚለው መከራከሪያ፤- እንኳን እኛ “ትግራይ በወያኔ ዘመን  አልተጠቀመችም የሚሉትንም ጭምር “ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ተደግፎ ለ17አመት ተዋግቶ አሸናፊ ሆኖ መውጣቱ አልካዱም።

በዚህ ከተስማማማን ወደ እሚቀጥለው ጉዳይ እናምራ። ደጋፊ ነበር ግን ዛሬ ትቶታል፤ ሲሉም መቸ ከድጋፉ እራሱን ነፃ እንዳደረገ አልነገሩንም። ዜጎች በደል ደርሶብናል ማለት እንደማስረጃ የቀረበው ቪዲዮም ቢሆን ወያኔዎች ጫካ ውስጥ  እያሉም በእሳት እየተጠበስን፤ እየተገረፍን፤ንብረታችን እየተወረሰ “በደል” ደርሶብናል፤ ‘ልጆቻችን’ ወደ ኤርትራ አትላኩዋቸው፤ እገሌ የተባለ ካድሬ/የሕዝብ ክፍል በደል አደረሰብኝ ......የሚሉ እሮሮሮዎች ሲያስሰሙ ነበር። እሮሮው ድሮም ዛሬም ያለ እና ሊኖር የሚችል በጨቋኞች ስርዓት ሊሰማ የሚችል እውነታ ነው። ያ እሮሮና ግፍ ግን ወያኔን ለ17 አመት መደገፍ አላቆማቸውም። ያ ደግሞ ምክንያት አለው። እየተዋጉት የነበረው በወያኔዎች ተፈብርኮ ለሕዝቡ የተሰበከ በትግራይ ሕዝብ “አማራ” የሚል ስም ሲጠራ የነበረው “የደርግ” ስርዓት በኤርትራኖችና በትግሬዎች “ወራሪ” ተብሎ ስለተደመደመ ትግራይን በ1ኛ 2ኛ 3ኛ .....7ኛ ወራር እየተባለ “በወረራ” የተጠረው ጦርነት መካላከል ስለነበራቸው እሮሮ ቢኖራቸውም ደግፈውታል። ዛሬም ይደግፋሉ። ማስረጃየን ላቅርብ።

ሕዝቡ ጸረ አማራነት ተቀርጾ አያውቅም፤ ሕዝብ አንድን ሕዝብ አይጣላም ብለው ለሚከራከሩ ሰዎች በኔ ሳይሆን ድርጅቱን ‘ሀ’ ተብሎ ሲጀመር ወደ ደደቢት ከወረዱት የመጀመሪያዎቹ 11 (12) ሰዎች አስገደ ገብረስላሴ (የታጋዮች የመጀመሪያ ወታደራዊ አሰልጣኝ የነበረ) እንዲህ ሲል ነግሮናል፡-

<<የጠባብ ብሔረተኛነት በሽታ በመላዋ ትግራይ እንደ ተላላፊ በሽታ ተስፋፍቶ ወደ ሕዝቡ በመተላለፉ አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ፀረ አማራ ተንቀሳቀሰ።” (አስገደ ገብረስላሴ ጋህዲ ቅ/2 ገ9/ 155 የትግርኛ ቅጂ 2001) (ትርጉም ጌታቸው ረዳ ይድረስ *ለጎጠኛው መምህር ገጽ 17 ደራሲ ጌታቸው ረዳ) (156)*

በወያኔ ካድሬዎች ትምሕርትና ቁጥጥር ስር ያለው ሕዝብ ወያኔን ይጠላል (አይደግፍም) ብሎ ማለት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩ እና ወያኔን እየተቃወሙ እስር ቤት የሚታሰሩ እነ አብርሃ ደስታ (የዓረና መሪ) የማሳሰሉ የትግራይ ምሁራን ሳይቀር "በሸዋ አማራ" ገዢነት በትግሬዎች የሚጠሩት ለነ አፄ ምኒልክ ሳይቀር ከፍተኛ ጥላቻ ያላቸው ሰዎች የተፈለፈሉበት አካባቢ ነው። አብርሃ ደስታ ከመለስ ይልቅ አስበልጦ አጼ ምኒልክን እንደሚጣላ ነግሮናል።

አብርሃ ደስታ እንዲህ ይላል።

<<ምኒልክ ጸረ እኩልነት ነው። ምኒልክ ለኔ ከመለስ በላይ አረመኔ ነው። የመተቸት መብቴ ሊከበርልኝ ይገባል።"(አብርሃ ደስታ) *(ከፌስ ቡኩ የተገኘ፤ ምንጭ የትግራይ ብሔረተኞች በአማራ ላይ ያላቸው ጥላቻ መነሻው ምንድ ነው? ከሚለው መጽሐፍ- ደራሲ ጌታቸው ረዳ*)

እንግዲህ እነዚህ ምሁራን ያውም በተቃወሚ የሚታወቁ እንዲህ ሲሉ የተቀረው ምን ይላል? እነዚህ ሰዎች ገጠሬው እና እነሱን የሚከተሉ የፖለቲካ አባሎቻቸው (ሕዝብ) እንዲህ ያለ ጥላቻ ሊያስትምሩት አይችሉም፤ ብሎ የሚል ሰው ካለ ይንገረኝ። አብርሃ ደስታ ስለ ትግራይ ሕዝብ ከተቃዋሚ ሆኖ ወያኔን ለመቃወም ያልፈለገበት ምክንያት እንዲህ ይገልጸዋል።

**<< *ወያነ 'ፀረ ደርግ' የነበረ ትግል 'ፀረ ኣማራ' እንደሆነ ኣድርጎ ኣቀረበልን። (በኣንደኛ ደረጃ ትምህርታችን ሳይቀር ተምረነዋል።)>> (ቃለ መጠይቅ አብርሃ ደስታ) (የትግራይ ብሔረተኞች መጽሐፍ ገጽ 393- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)* <<<< ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የሰርዓቱ ተቃዋሚዎች ህዋሕቶች "ደርጎች" ናቸው ስለሚሉዋቸው፤ ደርግ ደግሞ በትግራይን ህዝብ ጠላት ተደርጎ ነው የሚወሰደው (በፈፀመው ግፍ)። የትግራይ ህዝብ ያን የደርግ ኣገዛዝ ኣይፈልግም። 'ደርግ ይመለሳል' ከተባለ ታድያ (ማመዛዘን ቢያስፈልግም) ህዝቡ ከደርግ ህወሓትን መምረጡ እንዴት ይቀራል?>><u>አብርሃ ደስታ *(የትግራይ ብሔረተኞች መጽሐፍ ገጽ 393-
ደራሲ ጌታቸው ረዳ)*</u>**

**<<የትግራይ ህዝብ ህወሓትን ሲቃወም ከተቃዋሚዎች ጎራ እንደተሰለፈ ይቆጠራል። *ተቃዋሚዎች ደግሞ 'ደርጎች' መሆናቸው ነው ለህዝቡ ሲነገር የቆየው።* ስለዚ ኣንድ ሰው (ወይ ብዙ ሰዎች) ህወሓትን ከተቃወመ ከደርግ ጋር እንደተባበረ ነው የሚቆጠረው። በትግሉ ወቅት ከደርግ ጋር የተሰለፈ ሰው ምን ዓይነት ቅጣት ይሰጠው እንደ ነበር ህዝቡ በደምብ ያውቃል። ስለዚ የትግራይ ህዝብ 'የመቃወም ቅጣት' ይፈራል። ፈርቶም ... ሲጨቆን ዝም ይላል (የባሰ ኣታምጣ ወይ ብሎ የሕልፎ ብሎ)።>>አብርሃ ደስታ <u>*(የትግራይ ብሔረተኞች መጽሐፍ ገጽ 393- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)*</u>**

**ተቃዋሚዎች የትግራይን ህዝብ በሙሉ ህወሓትን እንደሚደግፍና 'ጠላት' እንደሆነ ኣስመስለው እንደሚያቀርቡ በብዙ የትግራይ ተወላጆች (በህወሓት ፕሮፓጋንዳ ምክንያት) ይታመናል። ይህንን እምነታቸው ህወሓትን የሚጠቀመው "ተቃዋሚዎች ደርጋውያን ናቸው፣ ደርግ ሙሉ በሙሉ ሞቶ ስላልተቀበረ ህወሓት እስከኣሁን ድረስ**

**ከደርግ ጋር እየተዋጋ ነው ወዘተ" የሚል የማጭበርበር ፕሮፓጋንዳ ለመቀበል ይገደዳሉ። በዚህ መሰረት ህወሓትን እየተቃወመም ቢሆን የተቃዋሚ ድርጅቶች ግን ከህወሓት ሊብሱ ይችላሉ ብሎ እንዲያስብ ስለሚገደድ ግራ ተጋብቶ 'የባሰ ኣታምጣ' ብሎ ኣብሮ ዝም ይላል።** ***(አብርሃ ደስታ) (የትግራይ ብሔረተኞች መጽሐፍ ገጽ 393- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)***

ከላይ በማስረጃ እንድታዩት ያደረግኩት ምንጩ ትግራይ ውስጥ የሚኖር በመታሰርና በመፈታት የተነገላታው የዓረና ፓርቲ ሊቀመንብር አብርሃ ደስታ ነው። ከማንኛውም ተከራካሪ ጉልህ ማስረጃ ሆኖ የምናየው ደግሞ ይህ ነው። ይህ ክርክር ደግሞ የሚያሳያን እርስ በርሱ የተምታታ መሆኑን ነው። የትግራይ ሕዝብ ወያኔን እንዳይቃወም ምክንያቱ ሲገልጽ ትግራይ ውስጥ 'ተቃዋሚ' መሆን ማለት 'ደርግ' ማለት ነው ስለሚያስብል፤ ተቃዋሚውን ከመደገፍ ይልቅ 'ስርዓቱን' መደገፍ' እንደደሚመርጥ ነግሮናል። በደርግና በወያኔ መካካል የተነጻጸረበት ምክንያት ሲገልጽ "ተቃዋሚ ማለት ደርግ ርዝራዦች" ተብሎ ስለተነገረው ደርግ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ጠላት ስለሆነ፤ ከዚህ በተጨማሪ ደርግ ማለት 'አማራ' ነው ተብሎ ሕዝቡ ስለተነገረው እና እሱ እራሱ አብርሃ ደስታም ከ፤ኛ ክፍል ጅምሮ ያሉት ህጻናት 'ደርግ ማለት አማራ ማለት ነው" የሚል ትምህርት እንደተሰጠ እና እሱም እራሱ ይህንኑ ት/ቤት ውስጥ እንደተማረ ገልጿል። ስለዚህ በተዘዋዋሪ የትግራይ ሕዝብ ጸረ አማራ ስሜት እንዳለው ነግሮናል ማለት ነው። ስለሆነም አማራ እንዳይመለስ በሚል ምክንያት ሕዝቡ የስርዓቱ ደጋፊ አልሆነም ማለት እንዴት ይቻላል? እንዲያምን ተደርጓል። ይህ ፕሮፓጋንዳ ከተቀበለ 'አማራ ተመልሶ እንዳይመጣ' ስርዓቱን ላለመቃወም መርጧል። ስለዚህ የተከራካሪዎቻችን እቅጩን መልስ እና የክርክራችን ጭብጥ እውነታውን እዚህ ታገኙታላችሁ።

*የተምታታ መሆኑን የገለጽኩት ነጥብ አስምሬ ልልፍ።*

አብርሃ ደስታ እንዲህ ይላል፤-

**<<በተመሳሳይ መልኩ በትግራይ የሚፈፀሙ ችግሮች፣ በደሎች፣ ጭቆናዎች የሚዘግብና የሚያጋልጥ ሚድያ የለም። በፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚድያ ሚና የማይናቅ ነው። በትግራይ ያሉ ችግሮች በኣግባቡ ስለማይዘገቡ ሰሚ ኣያገኙም። ሰሚ ካላገኙ (1) ሰዎቹ ተቃውመው ምንም ለውጥ ሊያመጡ እንደማይችሉ ስለሚረዱ እየተጨቆኑም ዝም ብለው ዝም ይላሉ፤ (2) ካልተዘገቡ በሌሎች ህዝቦች በትግራይ ችግር እንደሌለ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ስለዚህ ገዢው ፓርቲ ዓፈናን ለመሸፈን ዓፈናን (ራሱ) እንደመሳርያ ይጠቀመዋል። እንደውጤቱም በትግራይ ተቃውሞ እንኳ ቢኖር ስለማይዘገብ ግን ህዝቡ ህወሓትን እንደሚደግፍ ወይ እንደማይቃወም ተደርጎ ይወሰዳል። ትልቁ ችግር ይሄ ነው።** ***አብርሃ ደስታ (151) (የትግራይ ብሔረተኞች መጽሐፍ ገጽ 393- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)***

ተቃውሞ አለ፤ ግን የሚዘግፍ ዘጋቢ ስለሌለ ሕዝቡ ስርዓቱን እንደማይቃወም ተደርጎ በተቃዋሚዎች ይወነጀላል፡ ባለበት ክርክሩ፤ ተመልሶ እራሱ የተናገረው ተቃውሞ አለ ግን ዘጋቢ ታጣ ባለበት አንደበቱ እንዲህ ሲል ሲያፈርሰው እናደምጣለን ፤

<<**ስለዚህ ኣንድ ሰው (ወይ ብዙ ሰዎች) ህወሓትን ከተቃወመ ከደርግ ጋር እንደተባበረ ነው የሚቆጠረው። በትግሉ ወቅት ከደርግ ጋር የተሰለፈ ሰው ምን ዓይነት ቅጣት ይሰጠው እንደ ነበር ህዝቡ በደምብ ያውቃል። ስለዚ የትግራይ ህዝብ 'የመቃወም ቅጣት' ይፈራል። ፈርቶም ... ሲጨቆን ዝም ይላል፤የባሰ ኣታምጣ ወይ (ብኡ የሕልፎ ብሎ)።**>>አብርሃ ደስታ (148) ***(የትግራይ ብሔረተኞች መጽሐፍ ገጽ 393- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)***

ተቃውሞ አለ ሲለን ቆይቶ፤
<< **የትግራይ ህዝብ 'የመቃወም ቅጣት' ይፈራል። ፈርቶም ... ሲጨቆን ዝም ይላል፤የባሰ ኣታምጣ (ፈጣሪ በዛ ይብቃ ይበለን) ብሎ ሲጨቆን ዝም ይላል።**>>
ሲል በግልጽ ነግሮናል።

አሁን መጓቾቼም ሆነ ለአንባቢዎቼ የትግራይ ሕዝብ እንደሌሎቹ ለምን ወያኔን እንደማይቃወም ግልጽ እንደሚሆንላችሁ ተስፋ አለኝ። ሲጨቆን ዝም ካለ፤ "ሲቃወም እያየን አይደለም ተብሎ የሚቀርበው ክርክር ትክክለኛ ክርክር መሆኑን በዚህ ጭብጥ ማየት ትችላላችሁ።

ሌላውና የመጨረሻ ማስረጃየ ትግሬዎች ከታቃዋሚ ጋር ሆነው ስርዓቱን ለማፍረስ/ለመለወጥ ያልፈለጉበት ምክንያት እነዚህ ወንድሞች ካላወቁት ወደ ትግራይ ሄዶ የታዘበው የዓይን ምስክር የሆነው ታዋቂው ጋዜጠኛ ማሕሙድ ሱሌማን እንዲህ ሲል የነገረነን ሃቅ እዚህ ላቅርብና ልደምድም_

"ሆኖም መቀሌ በገዢው ፓርቲ ደስተኛ አትሁን አንጂ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ልቧን ከፍታ ፤ የሰጠችም፤ የምትሰጥም አትመስልም። በሐገሬው ዘንድ በህወሓት መጨከን በወለዱት መጨከን ተደርጎ ይታያል። ብዙ ታሪካዊ ምክንያቶች ሕዝቡ እንዲያ እንዲሆን አስችለውታል። የህወሓት እና የትግራይ ባንዴራ አንድ ናቸው። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር መሳ የህወሓት መዝሙር በትምህርት ቤቶች ይዘመራል።" "በሐገሬው ዘንድ በህወሓት መጨከን በወለዱት መጨከን ተደርጎ ይታያል። ብዙ ታሪካዊ ምክንያቶች ሕዝቡ እንዲያ እንዲሆን አስችለውታል። የህወሓት እና የትግራይ ባንዴራ አንድ ናቸው። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር መሳ የህወሓት መዝሙር በትምህርት ቤቶች ይዘመራል።" ይላል (መሐመድ ሱቅ ላይ ጠብቂኝ ከሚል የተገኘ ምንጭ)

## ክፍል አንደን ለማጠቃለል፡

ትግሬዎች ስንል፤ *በሙሉ ትግሬዎች* እያሉ "ሂፒክሪት" የሆነ ለክርክሩ ማምለጫ ሀረግ እየመዘዙ "መላው የትግሬ ተጠቃሚ አይደለም፤ተጠቃሚዎች ጥቂቶች ናቸው፤መላው ትግሬ ስልጣን ላይ አይደለም፤ ስልጣን ላይ ያሉት ጥቂት ናቸው" ሲሉ እንደ እነ አቤ ተኩቻውና ዶ/ር አወል የመሳሰሉ ከመከራከሪያ ነጥብ ለመሸሽ የሚያቀርቡት "መላውን ትግሬ" እያሉ እያሰመሩ የሚከራከሩት ክርክር ሰንጥቀን ማየት ያስፈልጋል።

እንዲታወቅልኝ-የምፈልገው፤ገጠር ውስጥ ያለውና የፖለቲካ እውቀት የሌላቸው ወላጆቻችን እና ትምህርት ዕድል ያላገኙ እናቶቻችን እህቶቻችንን፤ ስልጣን ላይ ባይኖሩም ልጆቻቸው ዘመዶቻቸው እና አቅፈው ደግፈው ለስልጣን የደረሰዋቸው ታጋዮች ስልጣን ላይ አሉ። ሁሉም ትግሬ ስልጣን ላይ ማውጣት እንደማይቻል እያወቁ፤ 'ሁሉም ትግሬ ' የምትለዋን ሐረግ እየመዘዙ እውነታውን በቃላት እየተጫወቱ እውነታውን በቃላት ተከልለው ለመደበቅ ይጥራሉ"። ጥቂቶች ሲሉን ጥቂት ማለት ስንት ነው? ስርዓቱን የሚያንቀሳቅሱ ያሉ ዋና ዋና መዋቅሮችና ቅርንጫፎች ስንት ናቸው? በነዚህ መዋቅሮች ውስጥ ማን አዛዥና ናዛዥ ተቀምጦባቸዋል? ጥፋት አላቸው የተባሉት እነ አባይ ወልዱ እና በርካታ ትግሬዎች ወደ አምባሳደርንት ሲሾም 'ሿሚው" ማን ስለሆነ ነው? ቤተክሕነቲቱ ሁለት ትግሬዎች ተፈራርቀው ገዝተዋታል። ሌላ ነገድ ብቃት ስለሌለው ነው? ማንስ ነው ተከታታይ ትግሬዎች እንዲመርዋት የሚያዘው የሥርዓቱ ጌቶች? ትግሬዎች! አይደሉም እንዴ? ተከራካሪዎቻችን ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት እነዚህ "ውር.. ውር" በሚሉ የመገለጫ ቃላቶች የሚገለጹ ናቸው?

ትግራይ ውስጥ ለሠርግ ጥሪ ሲደረግ ወደ ሠርጉ የሄዱት ቤተሰቦች "ስማቸውን" ስያስመዘግቡ "የእገሌ ቤተሰብ" ተብሎ ይመዘገባል። ወደ ሰርጉ የሄዱት ግን ባልና ሚስት ወይንም ባል ብቻ ሊሆን ይችላል፤ በዛ ቤተሰብ ውስጥ እህት፤ ልጅ ምናምን አለ፡ ሰርግ መኖሩንም የማያውቁ፤ ግን በነሱ ስም አብሮ "የእገሌ ቤተሰብ" ተብሎ ይመዘገባል። ሠርጉ ላይ ተገኝቶ የበላውም ያልበላውም፤ የተገኘውም ያልተገኘውም። በዚህ ትንተና ሕዝብ ተጠቃሚ ነው ሲባል መላው ሕዝብ ማለት አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓድዋ ላይ ጣሊያንን ድል ነሳ! ሲባል እኮ (በማይጨው ጦርነትም) መላው ሕዝብ ወደ ዓድዋ ሄዶ አልተዋጋም። የተዋጉት ከሚሊዮን ሕዝብ መካካል ጥቂቶች ናቸው። አምቢ ብለው የቀሩም ከጠላት ጋር ሆነው የተዋጉም ነበሩ። ሆኖም እነሱንም ጨምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓድዋ ላይ ጣሊያንን ድል ነሳ! ተብሎ ይነገራል። ጦር ሜዳ ላይ የተካፈሉ ዘማቾች ሁሉንም ነገዶች አልወከሉም ነበር። "ሕዝብ" ስንል እኮ በማንኛውም ታሪክ ሁሉም በነቂስ አይደግፍም፤ አይተኛም፤ አይዋጋም፤ አይበላም፤ አይጠጣም፤ ሥራ አያገኝም፤ አይሞትም፤ አይስቅም፤ አይዘፍንም፤ አይጨፍርም። በሙሉ የሚባለው ትርጉም በተለምዶ ስለሆነ እንጂ በሙሉ ሳይሆን ባብዛኛው ተጠቃሚ ሲሆን ማለት ነው (ለዓይን የሚታይ)። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግ/ጨዋ/አዛኝ ነው ሲባል "አጭበርባሪ ነብሰገዳይ ዘራፊ ጨካኝ" የለም ማለት አይደለም። ግን ብዙሃኑ ለማት ነው "ሕዝብ" ተብሎ የሚጠራው።

ተከራካሪዎቻችን ይህ 'ሂፐክርት' የቃላት ጨዋታ ባንጠቀም ጥሩ ነው።የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሚ ነው ስንል ብዙው የትግራይ ተወላጅ 'አዎ ተጠቃሚ ነው"። ትግራይ ውስጥ የተተከሉት ሚክሮ እና ማይክሮ ስትራክቸሩን (የምጣኔ ሃብት ጉልበተች) በምን መልኩ እነደተገነባ ማየት ነው። አገሪቱን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን ምጣኔ ሃብት ጎልቶ የሚታይ "የንግድ ተቋሞች" ባለቤቶች "ትግሬዎች" ናቸው። ወያኔዎች ናቸው። ወያኔዎች ደግሞ ትግሬዎች ናቸው። The pillage of Ethiopia by Dr. Assefa Negash እና ምጽአተ አማራ የሚባሉ ሁለት መጻሕፍቶችን ያንብቡ። የትግራይ ተጠቃሚነት በተጨባጭ ሰነዶች የተዘገቡ እውነታዎች እዛው ይገኛል።

*ትንሽ ማስረጃ ልጥቀስ፤-*

<< *አጎራባች ክፍለ-ሀገሮች አውራጃዎችና ወረዳዎች ወደ ትግሬ በማጠቃለል የተከናወነ ትግራይ ጠቀም ተግባር በወያኔ ዘመን “ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ” ወይንም “ክርስቶስ ለሥጋው አደላ” ሆኖባቸው... ከጎንደር ክ/ሀገር ሠቲት ሁመራን፤ጠገዴን፤ወልቃይትን፤ ጠለምትን፤ከፊል ታች አርማጭሆ እና ላይ አርማጭሆ ወረዳዎችን፡- ከወሎ ደግሞ “ራያና ቆቦ... አውራጃን ወደ ትግራይ በሃይል ማካለሉን ይታወቃል።በነዚህ አውራጃዎች እና ወረዳዎች ይኖሩ የነበሩ  አማሮች እና የሌሎች ነገዶች ተወላጆችን በልዩ ልዩ ሰበቦች በመግደል፤ በማሰር፤ በመሰወር፤ በማባረርና በማስገደድ፤ በምትካቸው የትግራይ ተወላጆች ሰፍረውበታል።*

*በነገራችን ላይ በስፋት የአማራ ዘር ማጥፋት ተግባር የተከናወነው በነዚህ የጎንደር ክ/ሀገር አካል በነበሩ፤ ዛሬ ግን የትግራይ አካል በሆኑ ወረዳዎች ኗሪ በነበሩ ነባር  የዐማራ ነገድ ተወላጆች ላይ ነው። በግልጽ እንደሚታወቀው፤ ወያኔዎች በትጥቅ ትግል ዘመናቸውና ከኤርትራ ጋር ባደረጉት ጦርነት የተጎዱ የወያኔ አባሎች “ጂ.ቲ.ዜድ” በተባለ የጀርመን ድርጅት የተገነባው “አውሮራ” የተሰኘው መንደር ወልቃይት ‘ወረዳ ዳንሻ’ ከተሰኘው ለምና ቁልፍ ወታደራዊ ቦታ ላይ ነው።ከዚህ ቦታ እንዲሰፍሩ የተደረጉት የወያኔ የሠራዊት አባሎች በትውልድ ትግሬ ከመሆናቸውም ሌላ ገበሬዎች ናቸው። የሠፋሪዎቹ የወያኔ የጦር ጉዳተኞች ዓይነተኛ ተልዕኮም፤ በሠፈሩባቸው አካባቢዎች ነዋሪ የነበሩ የሌሎች ነገድ ተወላጆች፤በተለይም አማራውን ከአካባቢው በልዩ ልዩ መንገዶች ማፈናቀል፤ መሬቱን መቀማት፤ የአካባቢውን ጸጥታ መቆጣጠር፤የሥለላ ሥራ መሥራት፤ የአካባቢውን የሕዝብ አሠፋፈር ‘ትግራይ ጠቀም’ ማድረግ የሚሉ ናቸው። በዚህ መሠረት ትናንት የዐማራ ‘አንጡራ-አጽመ ርስት’ የነበሩ የሠቲት፤የወልቃይት፤ የጠለምት፤ የማጠቢያና የቋራ ለምና ድንግል መሬት፤ የሰሊጥ፤ የጥጥ፤የዱር ሙጫ፤ የሚሽላ፤ የዘንጋዳ ባለቤት የነበሩት ሠፋፊ እርሻዎች፤ በትግሬ ገበሬዎችና “ኢንቬስተር” ነን ባይ ትግሬዎች ተወስደዋል ። በተመሳሳይ ሁኔታ በራያና ቆቦ አውራጃ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሌሎች ነገድ ተወላጆችንም በማፈናቀል፤ መሬቱ ተጠቃሚ የትግሬ ገበሬ ተወላጅ ሆኗል። በዚህ ድርጊት የትግሬ ሕዝብ አልተጠቀመም አንልም።* >>

*ምንጭ- “ምጽአተ ዐማራ - ተገድሎና ተገዳድሎ የማያልቅ ተነቅሎ የማይደርቅ በ2009 ዓ.ም ዋሺንግተን የታተመ” ገጽ 587 (በሞረሽ ወገኔ ድርጅት የታተመ መጽሐፍ) ድጋሚ ማስረጃ “የትግራይ ብሔረተኞች በአማራ ላይ ያላቸው ጥላቻ........በሚል መጽሐፍ ለማስረጃ የቀረበ - ደራሲ ጌታቸው ረዳ)።*

*በዚህ ሁኔታ የትግራይ ሕዝብ በፍትሕ እጦት አዎ እየተንገላታ ነው። ግን በፍትሕት የመንገላታቱ ሁኔታ የሥርዓቱ ባሕሪ ስለሆነ ፍትሕ ባለመኖሩ ግን የገዛ ልጁን (ትግራይን በፍትሕ እጦት እየቀጠቀጠ) እያንገላታ ነገር ግን በሌላ በኩል ከሌሎች ነገዶችና ልጆች አፍ ንብረትም ሆነ መሬት እየነጠቀ ለልጆቹ የሚያጎርሰውን እጅ እና ጎራሹ አይገናኙም ማለት አንችልም*

*ዛሬ ካፒታሉ/ሃብት፤ ንብረት፤ መሬት፤ ፋብሪካ ፤ባንክ፤ መአድን፤ በማን እጅ ነው? ድሆችና የተገፉ የሚባሉት የሚገደሉ፤ በነገዳቸው ምክንያት ከሥራ የሚባረሩት፤ የሚታሰሩት፤ ታስረው ሲደበደቡ በነገዳቸው “ሸንታም አማራ” እየተባሉ የሚሰደቡ እነማን ናቸው? ዳኛው፤ አሳሪው፤ ደብዳቢው ማን ነው? ብዙሃኑ የሚባሉ ድሆች እነማን ናቸው?*

ፖለቲካው መዘውሩ በማን እጅ ቁጥጥር ነው? ከዚያ መዘውር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ማን ነው? ይህ ሁሉ ስታዩ በትግሬ ተወላጆች መሆኑን ማየት ትችላላችሁ።

"…we are not really fighting the government; we are fighting against the entire system"- (Steve Biko in an interview with Greg Lanning, June 5, 1971.)

ተቀዋሚዎች የሚታገሉት ስርዓቱን ብቻ ሳይሆን በመኖሞፖሊ የተያዙትን ኢኮሚያዊና ፖለቲካዊ መዋቅሮችን ኢፍትሓዊ መደላድል ስላልሆነ ያንን ማፍረስ ነው ትግላቸው። አፓርታይድን ስትቃወም በንብረት ላይ ያለው ጉልብት እኩል ካልተከፋፈለ ስርዓቱ አድሎአዊ ነውና መፍረስ አለበት። ደቡብ አፍረካ እዩየሆነ ያለው ያ ነው። ስር ቱ ቢፈርስም ምጣኔ ሃብቱ ዛሬም በነጮች እጅ ስለቀረ ጉልበቱ አሁን አለ። የትግሬዎች ስር ት ሲለወጥም ፤ ምጣኔ ሃብቱ ፤ፋብሪካው አሴቱ ለአገሪቱ ገቢ ካልሆነ የበላይነቱ በትግሬዎች እጅ መቆየቱ አይቀሬ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔ መንግሥት ሲገረሰስ ግን 'ትቶት የሚሄድ የስርዓቱ/ የሲስተሙ" ቅሪት እንደ አፓርትዋ ደ/አፍሪካ በዘመነ ወያኔ ሐብታም ሆነው ንብረቱን እና መሬቱን፤ ቤቶችን፤ ባንኮችን፤ አስመጪና ላኪ ተቋማትን፤ ኩባኒያዎችን፤ መገናኛ አብዮብሶችን… የተቆጣጠሩ ወገኖች (ትግሬዎች) በተቀረው ድሃ ሕዝብ ሕይወት ላይ "ቀጣይ" ወሳኞች ሆነው ይቀጥላሉ።

<< ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ ከመቶ ዘመናዊ የግል አውቶሞቢሎች ለወያኔዎች በሚያዳላ አነስተኛ ግምት ስልሣው የትግሬ ነው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚታዩ መቶ ታላላቅ የግንባታ ሥራዎች መካከል ዘጠና አምስቱ የትግሬ ናቸው– ለምን እንዋሻለን? ከትግሬዎች ጋር ምንም ዓይነት ውድድር የለም፤ እነሱ ሁሉ በኛቸው ሁሉ በደጃቸው ነው – ያለቀረጥ ይነግዳሉ፤ ያለቫት ይነግዳሉ፤ ያለቤት ኪራይ ይነግዳሉ፤ ያለ ፍትህ ያስፈርዳሉ፤ እነሱ ገድለው ሟችን ይከሳሉ፤ እነሱ ዘርፈው በተጠቂነት ምስኪኖችን ይከስሳሉ፡፡ በጥቅሉ ኢትዮጵያና ሕዝቧ በነሱ ታግተው በስቃይ እየማቀቁ ናቸው፡፡የማውቃት አዲስ አበባ ወዴት ሄደች ብለህ ብትጠይቅ መልሱ በመቀሌ ተዋጠች ነው – መቀሌን ሆነች" (ምህረት ዘገየ፡- አትዮ-ሰማይ ድረገጽ የተለጠፈ መጣጥፍ) >>(ምንጭ ጌታቸው ረዳ የትግሬ ብሔረተኞች መጽሐፍ።)

ይህ የወልድያ እናቶች እምባ ትግራይ ውስጥ ይታያል? እስቲ ይህንን ተመለከቱልኝ እና ፍረዱ፡-

**የወልዲያ እናቶች እንባ** https://youtu.be/5Oci1Ew8le8

የትግራይ ሕዝብ ከወያኔ የነገድ ፖለቲካው ጋር ያላቸው ዝምድና ምንድ ነው የሚሉትን በክፍል ሁለት ይቀጥላል፡……. getachre@aol.com

ጌታቸው ረዳ (የትግራይ ብሔረተኞች…… ደራሲ )